# የዘወትር ጸሎት

አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል (3ጊዜ በል):: በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ በቅድስት ሥላሴ እንዘ አአምን ወእትመሐፀን እክሕደከ ፀርየ ሰይጣን በቅድመ ዛቲ እምየ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ይእቲ ስምዕየ ማርያም ጽዮን ለዓለመ ዓለም::

አንድ አምላክ በሆኑ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ንጹሕ ልዩ ክቡር ጽኑይ በሆኑ በሦስትነት ወይም በሥላሴ እያመንኩና እየተማፀንኩ ጠላቴ ሰይጣንን እክድሃለሁ ፣ በዚች በእናቴ በቤተክርስቲያን ፊት ቆሜ እክድሃለሁ ፣ ለዚህም ምስክሬ ማርያም ናት:: በዚህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም እሷን አምባ መጠጊያ አድርጌ እክድሃለሁ::

I cross my face and all of myself by the sign of the cross. In the name of father, and son and the Holy Sprit one God AMEN. In the Holy Trinity believing and entrusting myself, I deny you satan in front of my mother the Holy Church, who is my witness, St. Mary Tsion forever. AMEN

ነአኵተከ እግዚኦ ወንሴብሐከ ንባርከከ እግዚኦ ወንትአመነከ:: ንገኒ ለከ እግዚኦ ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ:: ንሰግድ ለከ ኦ ዘለከ ይሰግድ ኵሉ ብርክ ወለከ ይትቀነይ ኵሉ ልሳን:: አንተ ውእቱ አምላከ አማልክት ወእግዚአ አጋዕዝት ወንጉሠ ነገሥት አምላክ አንተ ለኵሉ ዘሥጋ ወለኵላ ዘነፍስ ወንጼውዐከ በከመ መሐረነ ቅዱስ ወልድከ እንዘ ይብል አንትሙሰ ሶበ ትጼልዩ ከመዝ በሉ::

አቤቱ እናመሠግንሃለን፣ አቤቱ እናከብርሃለን፣ አቤቱ እንገዛልሃለን፣ አቤቱ ቅዱስ ስምህን እናመሰግናለን፣ ጉልበት ሁሉ የሚሰግድልህ አቤቱ እንሰግድልሃለን፣ አንደበትም ሁሉ ለአንተ ይገዛል፣ የአምላኮች አምላክ፣ የጌቶች ጌታ የንጉሦችም ንጉሥ አንተ ነህ:: የሥጋም የነፍስም ፈጣሪ አንተ ነህ:: እናንተስ በምትጸልዩበት ጊዜ እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ ብሎ ቅዱስ ልጅህ እንዳስተማረን እንጠራሃለን::

We thank you Oh Lord, and we glorify you, we praise you Oh Lord, and we rely on you, we beg you and we beseech you. We worship you and we serve to your Holy name. We bow and kneel down to you; oh you to whom all knees should bow and who all tongues serve. You are the God of gods and the Lord of lords and the king of kings. You are God to all flesh and to all souls, and we call you as your Holy Son taught us saying "But when you pray you shall say", Our Father who are in heaven…

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም:: ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ:: ኢትአብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት:: አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም:: አሜን::

አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን:: የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ በደላችንንም ይቅር በለን እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል:: አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይል ምስጋና ለዘለዓለሙ አሜን::

Our father who art in heaven, hollowed be they name, thy kingdom come, thy will be done in earth as it is in heaven: give us this day our daily bread and forgive us our trespasses as we forgive them that trespass against us, and lead us not into temptation but deliver us and rescue us from all evil: for thine is the kingdom, the power and the Glory for even and ever. AMEN.

በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ. ድንግል በኅሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ:: እመ እግዚአብሔር ጸባዖት ሰላም ለኪ:: ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ:: ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ:: ሰአሊ ወጸልዩ ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣዊኢነ::

እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ በሃሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ:: የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይገባል:: ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው:: ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርክቶስ ዘንድ ይቅርታን ለምኝልን ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ለዘለዓለሙ አሜን::

By the Salutation of the Saint Angel Gabriel, O my Lady Mary I salute you, thou are Virgin in thought, and Virgin in body the Mother of God Tsabaot. (The Lord of Hosts) salutation to you. Blessed art thou, among women and blessed is the fruit of your womb. Rejoice thou who is hailed, O Graceful God is with you. Beseech and pray for our mercy to you beloved Son JESUS CHRIST that he may forgive us our sins. AMEN

ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ዘሀልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም::

ሁሉን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን:: ሰማይና ምድርን የፈጠረ የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ አንድ የአብ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፤

We believe in one God, the father Almighty, maker of heaven and earth, and all things visible and invisible.

And we believe in one Lord Jesus Christ the only begotten son of the Father who was with him before the creation of the World.

ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን:: ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ:: ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ::

ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ በባሕርይው ከአብ ጋር የሚስተካከል ሁሉ በእርሱ የሆነ በሰማይ ካለው በምድርም ካለው ያለእርሱ ምንም ምን የሆነ የለም

Light from light, true God from true God, begotten not made of one essence with the Father.
By whom all things were made, and without him was not anything in heaven or earth made:

ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት ተሰብአ ወተሰገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ኮነ ብእሴ ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ:: ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማኑ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ::

ስለ እኛ ስለ ሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፍጹም ሰውን ሆነ ደግሞም ስለ እኛ ተሰቀለ:: በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን እርሱ መከራን ተቀበለ ሞተ ተቀበረ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ በክብር በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፤ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ በምስጋና ይመጣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም::

Who for us men and for our salvation came down from heaven was made man and was incarnate from the Holy Spirit and from the Holy Virgin Mary.
Become man was crucified for our sakes in the days of Pontius pilate suffered, died, was buried and rose from the dead on the third day as was written in the Holy Scriptures: Ascended in glory into heaven, sat at the right hand of his Father, and will come again in glory to judge the living and the dead; there is no end to his reign.

ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ ንሰግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለአብ ወወልድ ወነበበ በነቢያት:: ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባዔ ዘሐዋርያት:: ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም::

በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን እርሱም ጌታ ሕይወትን የሚሰጥ ከአብ የሠረፀ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለን እርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረው ነው:: ከሁሉም በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሠሯት በአንዲት ክብርት ቤተክርስቲያን እናምናለን:: ኃጢአት በሚሠረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ አሜን::

And we believe in the Holy Spirit, the life-giving God, who proceeded from the Father; we worship and glorify him with the Father, and the Son; who spoke by the prophets.

And we believe in one baptism from the remission of sins, and walt for the resurrection from the dead and the life to come, world without end, AMEN.

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያት ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ:: ንስግድ ለከ ክርስቶስ ምስለ አቡከ ኄር ሰማያዊ ወመንፈስከ ቅዱስ ማኅየዊ እስመ መጻእከ ወአድኃንከነ::

አሸናፊ እግዚአብሔር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለህ ትመሰገናለህ:: ምስጋናህም በሰማይና በምድር የመላ ነው:: ክርስቶስ ላንተ እንሰግድልሃለን ከሰማያዊው ከቸር አባትህ ጋር አዳኝ ከሆነው ከመንፈስ ቅዱስም ጋር እንሰግድልሃለን ወደዚህ ዓለም መጥተህ አድነኸናልና::

Holy, Holy, Holy God Tsabaot perfect Lord of Host, heaven and earth are full of the holiness of your Glory. We bow to you Christ, with your good heavenly Father and with your Holy Spirits the life Giver from thou didst come and save us.

እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐተ ስግደተ (ሥልሰ ጊዜያተ በል) እንዘ አሐዱ ሠለስቱ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ ሠለስቱ ወእንዘ ሠለስቱ አሐዱ እንዘ ይሜለሱ በአካላት ወይትዋሐዱ በመለኮት እሰግድ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ እሰግድ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተቀደሰ በደሙ ክቡር:: መስቀል ኃይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል ቤዛነ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ አይሁድ ክሕዱ ንሕነሰ አመነ ወእለ አመነ በኃይለ መስቀሉ ድኅነ::

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አንዲት ስግደት እሰግዳለሁ ፫ ጊዜ በል:: አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ አንድ በአካል ሦስት ሲሆኑ በመለኮት አንድ ለሚሆኑ እሰግዳለሁ:: አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ለድንግል ማርያምም እሰግዳለሁ:: ዓለምን ሁሉ ለማዳን ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ ለተሰቀለበት መስቀልም እሰግዳለሁ:: መስቀል ኃይላችን ነው፣ ኃይላችን መስቀል ነው:: የሚያፀናን መስቀል ነው፣ መስቀል ቤዛችን ነው፣ መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው አይሁድ ይክዱታል እኛ ግን እናምነዋለን ያመነው እኛም በመስቀሉ እንድናለን::

Let us bow down to the father, and the Son, and the Holy Spirit. Three in one and one in three. Three in person and united in Godhead. I bow down to our Lady St. Mary Virgin Mother God. I bow down to the cross of our Lord Jesus Christ which was sanctified by his precious Blood. The cross is our power, the Cross is our strength, the Cross is our redemption, the cross is the salvation of our soul. The Jews denied but we believe, and those who believe in the power of the Cross are saved.

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ (ሥልሰ ጊዜያተ በል):: ስብሐት ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ስብሐት ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በምሕረቱ ይዘከረነ:: አመ ዳግም ምጽአቱ ኢያስተኀፍረነ:: ለሰብሐተ ስሙ ያንቅሀነ ወበአምልኮቱ ያጽንአነ እግዝእትነ ማርያም አዕርጊ ጸሎተነ ወአስተሥርዪ ኃጢአተነ ቅድመ መንበሩ ለእግዚእነ ለዘአብልዐነ ዘንተ ኅብስተ ወለዘአስተየነ ዘንተ ጽዋዓ ወለዘሠርዐ ለነ ሲሳየነ ወአራዘነ ወለዘተዐገሠ ኵሉ ኃጢአተነ ወለዘወሀበነ ሥጋሁ ቅዱሰ ወደሞ ክቡረ ወለዘአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት::

ለአብ ምስጋና ይገባል፣ ለወልድም ምስጋና ይገባል፣ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል ፫ ጊዜ በል:: አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም ምስጋና ይገባል:: ለኢየሱስ ክርስቶስ መስቀልም ምስጋና ይገባል:: ክርስቶስ በቸርነቱ ያስበን ዘንድ ዳግመኛም በመጣ ጊዜ እንዳያሳፍረን ስሙን ለማመስገን ያነቃን ዘንድ እርሱንም በማምለክ ያጸናን ዘንድ እመቤታችን ጸሎታችንን አሳርጊልን ፣ ኃጢአታችንንም አስተሥርዩልን በጌታችን መንበር ፊት ጸሎታችንን አሳርጊልን ፣ ይህንን ኅብስት ሳበላን ይህንንም ጽዋ ሳጠጣን ምግባችንንና ልብሳችንን ሳዘጋጀልን ኃጢአታችንንም ሁሉ ለታገሠልን ክቡር ደሙን ቅዱስ ሥጋውን ለሰጠን እስከዚችም ሰዓት ላደረሰን

**Glory To The Father, Glory To The Son, Glory To The Holy Spirit (Three Times).** Glory to our Lady St. Mary the Virgin Mother of God. Glory to the Cross of our Lord Jesus Christ. May Christ in his mercy remember us. May he not put us to shame in his second coming. May he awaken us to the glorification of his name. in his worship may he maintain us. Our Lady St. Mary, lift up our prayer before the throne of our Lord, who gave us to eat this bread, and who gave us to drink this cup, and who prepared our food and our clothing for us, and who overlooked all our sins, and who gave us his Holy Body and his precious Blood, who brought us to this hour.

